# የጥበብ ሰዎች መጡ

ሰማይና መሬት የማይወስኑት
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት
ዘጠና ዘጠኙን መላዕክቱን ትቶ
አገኘነው ዛሬ ከበረት ተኝቶ

የጥበብ ሰዎች መጡ (፪)
ሰምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከብ እንደፋና

ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ
ካንቺ ተወለደ የአለም መድህን
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርሰን

አዝ...

ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም
ሃዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት

አዝ...

ሰብአ ሠገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእስራኤል ንጉስ ወዴት ነው እያሉ
እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየ ስርአቱ
እጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግስቱ

አዝ...

www.HolyTrinityEOTCNY.org